# A እና B የኗሪነት ቅጾች
# መመሪያዎች እና የአስፈላጊ ሰነዶች ማረጋገጫ ዝርዝር

የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) በጋራ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች በየትምህርት ዓመቱ ሁለት (2) የኗሪነት ማረጋገጫ ቅጾችን የአርሊንግተን የቤት አድራሻ ለማረጋገጥ ከሚያስፈልጉ ሰነዶች ጋር እንዲያቀርቡ ይጠይቃል።

1. **ቅጽ A-** የወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች የኗሪነት ማረጋገጫ ጽሁፍ
2. **ቅጽ B-** የአርሊንግተን ኗሪ ማረጋገጫ መግለጫ ጽሁፍ

እነዚህ የማረጋገጫ ወረቀቶች ቤተሰቦች ከአርሊንግተን የቤት ባለቤት ወይም የሊዝ ይዞታ ካለው ሰው ጋር እንደሚኖሩ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው። በአመት ውስጥ አንድ ቤተሰብ አንድ ጊዜ ቅጽ A እና ቅጽ B ብቻ ማጠናቀቅ አለባቸው። ይህ ከአንድ ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ ጋር የሚኖሩትን ወንድሞችና እህቶች ሁሉ ይመለከታል።

**<u>የአስፈላጊ ሰነዶች ማረጋገጫ ዝርዝር:</u>**

ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች፣ ወይም አዋቂ ተማሪዎች በሌላ ሰው መኖርያ ቤት ከልጃቸው ጋር በጋራ የሚኖሩ ከሆኑ፣ እነዚህ **አምስት (5) ሰነዶች ማቅረብ** አለባቸው፡-

- ☐ ቅጽ A- የወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች የኗሪነት ማረጋገጫ መግለጫ ጽሁፍ
- ☐ ቅጽ B- የአርሊንግተን ኗሪ ማረጋገጫ መግለጫ ጽሁፍ
- ☐ ስመርስት ወይም የአሁኑ የሊዝ ስምምነት
- ☐ ሁለት (2) ደጋፊ ሰነዶች (ዝርዝሩን ከስር ይመልከቱ)

**<u>ደጋፊ ሰነዶች፡-</u>**

**የወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ ወይም የአዋቂ ተማሪው ስም እና የአርሊንግተን አድራሻ ከ A & B ቅጾች ጋር የተጠቀሰው አድራሻ ጋር የሚዛመዱ ሁለት (2) ዋና እና የተለያዩ ደጋፊ ሰነዶች ከሚከተለው ዝርዝር ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡-**

- ☐ የአሁኑ የፌዴራል፣ የስቴት ወይም የንብረት ግብር ተመላሾች
- ☐ የቅርብ የክፍያ ጊዜ የሆነ የአሁን የደመወዝ ክፍያ ገላጭ
- ☐ የአሁኑ የተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ
- ☐ የቅርብ ጊዜ የሆነ የፍጆታ ክፍያዎች
- ☐ የአሁኑ አድራሻ ያለው የሚያገለግል የቨርጂኒያ መንጃ ፍቃድ ወይም በመንግስት የተሰጠ መታወቅያ
- ☐ በአሁኑ የዩኤስ ከፌዴራል፣ ከስቴት ወይም ከአካባቢ መንግስት የተሰጠ መታወቂያ
- ☐ የአሁኑ የባንክ መግለጫ
- ☐ የቤት ባለቤትነት ወይም የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ
- ☐ የመራጮች የምዝገባ ካርድ
- ☐ የአሁኑ የገቢ ግብር ቅጽ 1099 ወይም W-2

*እባኮትን እንደ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥሮች (Social Security numbers) ወይም የፋይናንሺያል ዝርዝሮች ያሉ የግል መረጃ የሚያሳዩ ማንኛውም መረጃ ከድጋፍ ሰጭ ሰነዶች መሰረዛቸውን ያረጋግጡ። APS እነዚህን ሰነዶች ስምዎትን እና አድራሻዎችን ለማረጋገጥ ብቻ ጥቅም ላይ ያውላል።*

**ጠቃሚ ምክር፡-** የድጋፍ ሰነዶችዎ ወቅታዊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፣ ለምሳሌ ከቅርብ ጊዜ የክፍያ አከፋፈል ዑደት የተገኘ የፍጆታ ክፍያ።

**<u>መመሪያዎች:</u>**

**ቅጽ A- የወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች የኗሪነት ማረጋገጫ መግለጫ ጽሁፍ፡-**

1. ወላጁ፣ ህጋዊ አሳዳጊው ወይም አዋቂ ተማሪው ይህንን ቅጽ ማጠናቀቅ እና መፈረም አለባቸው።
2. ፈቃድ ያለው ኖታሪ (notary) ቅጹን ኖተራይዝ ማድረግ አለበት።

**ቅጽ B- የአርሊንግተን ኗሪ ማረጋገጫ መግለጫ ጽሁፍ፡-**

1. ቤተሰቡ የሚኖርበት የቤቱ ባለቤት ወይም የሊዝ ይዞታ ያለው ሰው ይህንን ቅጽ ማጠናቀቅ እና መፈረም አለበት።
2. ፈቃድ ያለው ኖታሪ (notary) ቅጹን ኖተራይዝ ማድረግ አለበት።

**ሁለቱም የA እና B ቅጾች፡-**

- ከጁላይ 1 ጀምሮ እስከ የትምህርት አመቱ መጀመሪያ ባለው ጊዜ መካከል በየዓመቱ ኖተራይዝድ ተደርገው መቅረብ አለባቸው።
- የወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ ስም እና አድራሻ ያካተቱ ሁለት ደጋፊ ሰነዶች ያስፈልጋሉ።
- ለትምህርት ቤት ምዝገባ እና አመታዊ የቤት አድራሻ ማረጋገጫ ጥቅም ላይ ይውላሉ።
- ለአንድ የትምህርት አመት ብቻ ያገለግላሉ።

- **ጥያቄ ካልዎት ወይም እርዳታ ከፈለጉ፡-**
- • የትምህርት ቤትዎ መዝገብ ቤት ወይም
- • የአርሊንገትን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የእንኳን ደህና መጣችሁ ማእከልን በ 703-228-8000 (ምርጫ 1) በመደወል ወይም መስመር ላይ በwww.apsva.us/contact-aps/ ያግኙ።